# ከፓርቲዎች "ድርድር" ምን እንጠብቅ?

ሰለሞን ሽፈራው 03-06-17

ክቡር የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሙላቱ ተሾመ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን የ2009 ዓ.ም የስራ ዘመን በከፈቱበት ንግግራቸው ላይ፤ መንግስት በዚህ ዓመት ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ለመወያየት ማቀዱን ገልፀው እንደ ነበር አይዘነጋም፡፡ እናም ፕሬዚዳንቱ በዚያ የመክፈቻ ንግግራቸው የገለፁትን የመንግስት ዕቅድ መሰረት ያደረገ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ሰንበትበት ብሏል፡፡ ለአብነት ያህልም ኢህአዴግና ከ20 የሚበልጡ በሕጋዊ መንገድ የሚታገሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ በግንባር ተገናኝተው የድርድሩ ወይም የውይይቱ አጠቃላይ ሂደት ምን መምሰል ይኖርበታል? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ወደ አንድ ዓይነት ስምምነት ለመድረስ በሚያስችል የመግባቢያ ሃሣብ ላይ መክረው ዘክረው ይበጃል የሚሉትን አቋም ለመድረኩ እንዲያቀርቡ አምስት ሰዎች መመረጣቸው ይፋ መደረጉን ማስታወስ ይቻላል፡፡

እንግዲያውስ የዚህ ፅሁፍ ትኩረትም፤ ለመሆኑ በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚዎቹ መካከል አሁን ሊካሄድ የታሰበው ድርድር ዋነኛ ዓላማ በተሟላ መልኩ ግልፅ ተደርጓል ወይ? ከሆነስ የድርድሩ ቁልፍ ነጥቦች ምን-ምን ናቸው? እውን የአሁኑ መድረክ የፖለቲካዊ ችግሮቻችንን ሰንኮፍ ነቅሎ ለመጣል የሚያስችል የጋራ መግባባት ላይ የሚደረስበት ይሆናል ብለን ተስፋ እናድርግ? ወዘተ በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ የሚያጠነጥን ሃሳብ ማንሳትና ስለጉዳዩ አስፈላጊነት ያለኝን የግል ምልከታ ለመግለፅ መሞከር ነው፡፡

በዚህም መሠረት በድርድሩ የሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያቀረቧቸው አራት መሠረታዊ ነጥቦች የድርድሩ ዓላማ እንዲሆኑ ስምምነት ላይ ደርሰዋል። እነዚህ ነጥቦችም በድርድሩ ወቅት የሚነሱ የተለያዩ ነጥቦችን እንደ ግብአት በመጠቀም፣ መሠረታዊ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ሕጎች እና ድንጋጌዎች እንዲሻሻሉ ማድረግ፤ የፓርቲዎችን ዴሞክራሲያዊ የእርስ በእርስ ግንኙነት በማጠናከር ለሀገራችን ሠላም፣ ዴሞክራሲ እና ዕድገት የሚኖራቸውን ሚና ማጎልበት፣ ሕዝቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያቀርቡለትን አማራጭ ሁሳብ ተገንዝቦ በዕውቀት እና በመረጃ ላይ ተመሥርቶ ለመንቀሳቀስ የሚያስችለውን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤ የሀገራችንን የፖለቲካ ምህዳር ችግሮችን ነቅሶ

በማውጠት፣ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓቱ ዕውን እንዲሆን እና እንዲዳብር ማድረግ የሚሉት ናቸው ተደራዳሪ ፓርቲዎቹ የተስማሙባቸው።

ከዚህ አጠቃላይ ግንዛቤ አኳያ አንዳንድ ነጥቦችን እያነሳን ርዕሰ ጉዳያችንን ሊያዳብርልን የሚችል ሃሳብ እንለዋወጥ ዘንድ፤ በቅድሚያ መግለፅ የሚኖርብኝም፤ ድርድሩን በታቀደለት መልኩ እንዲካሔድ ለማድረግ የኢፌዴሪ መንግስትና እንዲሁም ደግሞ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ላሳዩት ተነሳሽነት ያለኝን አድናቆት ነው፡፡ ምንም እንኳን የፓርቲዎች ድርድር መድረኩን ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ እንዲገኝ በማድረግ ረገድ የአንበሳውን ድርሻ ሊወስድ የሚችለው ጉዳይ በተለይም የትምህክተኝነትንና የጠባብ ብሔርተኝነትን ፅንፈኛ አቋም ወክለው የሚንቀሳቀሱት አክራሪ የተቃውሞው ጎራ ፖለቲካ ሃይሎች ከመጋረጃው በስተጀርባ እየተቧደኑ የሚዶልቱት ፀረ-ሕገ መንግስት ሴራና ብሎም የሚፈፅሙት ደባ እንደሆነ ባይካድም፤ስርዓቱን ከማንኛውም ዓይነት የቅልበሳ አደጋ የመታደግ እርምጃ መውሰድ የሚጠበቅበት የኢፌዴሪ መንግስት አሁንም እንደተለመደው ሁሉ፤ ጉዳዩን በሆደ ሰፊነት የያዘበት አግባብ አድናቆት አይበዛበትም የሚል እምነት አለኝ፡፡

ይህን ስል ግን፤ ገዢው ፓርቲና መንግስት የድርድር መድረኩን በማዘጋጀት ረገድ ያሳዩት ተነሳሽነት ብቻውን፤ ስር-ነቀል የስርዓት ለውጥ ሒደቱን ለመቀልበስ ያለመ አመፃ ሴራ ሲያውጠነጥኑ እንቅልፍ አጥተው የሚያድሩ ነውጥ ናፋቂ ቡድኖችን ከተለመደው አፍራሽ ተግባራቸው እንዲታቀቡ ሊያደርጋቸው ይችላል ማለቴ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ፤ ለመላው የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዘለቄታዊ የጋራ ዕጣ ፈንታ መቃናት እንደሚበጅ ሀገራዊ መግባባት ላይ የደረስንበትን ሕገ-መንግስታዊ የቃል ኪዳን ሰነዳችን ባካተታቸው የሰላማዊ ትግል ማስፈፀሚያ ማዕቀፎች አማካኝነት የሚስተናገድ የመድብለ ፓርቲ ፖለቲካዊ ስርዓትን በተከተለ መልኩ የሚደረግ ዕርስ በርስ የመወያየትና ከተቻለም የመደማመጥ ጥረት እጅግ ጠቃሚ ነው ብሎ ማጠቃለል ተገቢ ይመስለኛል፡፡

ስለዚህ የመድረኩ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ድርድሩ የታለመለትን ግብ እንዲመታና በሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት ላይ ትርጉም ያለው አውንታዊ ተፅእኖ የሚያሳድር ድምር ውጤት እንዲያመጣም ጭምር፣ ከየአንዳንዱ ተሳታፊ የፖለቲካ ፓርቲ፤ እንዲሁም ደግሞ ከመላው ህብረተሰባችን ምን እንደሚጠበቅ ለመጠቆም ልሞክር፡፡ እንደኔ የግል ግንዛቤ ከሆነ፤ በዚህ የድርድር መድረክ ለመሳተፍ የተመዘገቡትን የፖለቲካ ፓርቲዎች በሶስት ከፍሎ ማየት እውነታውን በተሻለ መልኩ የሚገልፀው ይመስለኛል፡፡

ከዚህ አኳያ፣ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ የመጀመሪያውን ረድፍ ይይዛል ብንል፣ ሁለተኛውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ በፊታውራሪነት የሚመራቸው የብሔር ድርጅቶች፣ እንዲሁም ደግሞ ሶስተኛውን፣ እነ መ.ኢ.አ.ድና ሰማያዊ ፓርቲ የሚወከሉበት ጎራ ሊይዝ እንደሚችል ነው የሚሰማኝ፡፡ ታዲያ በዚህ መልኩ የሚያስፈርጃቸውን የሶስትዮሽ አቋም ከሚያራምዱት የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን ድርድር መጠበቅ የሚኖርብን ድምር ውጤት ምንድነው? ለዚህ ጥያቄያችን ምላሽ የሚሆን ሃሳብ ለመሰንዘር ይረዳን ዘንድ፣ ከላይ የተመለከቱትን ሶስት ጎራዎች የሚወክል የየራሳቸው ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ያላቸው ኢህአዴግና የእርሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ስለ አሁኑ ድርድራቸው ሂደት ዝርዝር አፈፃፀም መምከር - መዝከር ከጀመሩበት ቀን አንስተው በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች አማካኝነት ሲሰነዝሩ ከሚደመጡት የሶስትዮሽ ሃሳብ ለአብነት ያህል ማስታወስ ተገቢ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

እናም በዚህ ረገድ ለታሰበው ፖለቲካዊ ውይይት ዝርዝር አፈፃፀም ግብዓት ሊሆን ይችላል በሚል እምነት የየራሳቸውን መነሻ ሃሳብ ካቀረቡት ተቃዋሚ ፖለቲከኞች መካከል፣ እኔ በግልፅ የሰማሁት የሁለተኛውን ረድፍ የተቃውሞ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ይወክላል ያልነው፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክና እንዲሁም የገዳ ስርዓት አራማጅ ፓርቲ የተሰኘ ድርጅት ናቸው፡፡ በዚህ መሰረትም፣ የመድረክ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ፓርቲያቸውን ወክለው እንደመነሻ ሃሳብ ያቀረቡት የመደራደሪ ነጥብ "ሀገሪቷ ውስጥ የሚስተዋሉትን አጠቃላይ የፖለቲካ ችግሮች በዘላዊቂነት ለመፍታት የሚያስችለንን የዴሞክራሲ ምህዳር ስለመፍጠር ጉዳይ መወያየት እንፈልጋለን" የሚል ነው፡፡

"ለምሳሌ የምርጫ ሕጋችንን ብንወስድ እኛ ተቃዋሚዎች ፓርላማ ገብተን ድምፁን ለሰጠን ህዝብ የሚጠቅም ሃሳብ ማራመድ እንዳንችል አድርጎናል፡፡ በዚሁ ምክንያት ደጋፊዎቻችን ሁሉ ፓርላማ የማትገቡ ከሆነማ ለምን እንመርጣችሁአለን? ወደሚል ተስፋ መቁረጥ የደረሱበት ሁኔታ ስላለ ሕጉ መሻሻል ይኖርበታል" ሲሉም አክለዋል ፕሮፌሰሩ፡፡ የገዳ ስርዓት አራማጅ ፓርቲ በበኩሉ ወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል ከስራ አጥነት ችግር ሊታደግ የሚችል የመፍትሔ እርምጃ ስለመውሰድ ከገዥው ፓርቲ ጋር የመደራደር ፍላጎት እንዳለው አሳውቋል፡፡

እንደኔ እምነት ከሆነ፣ እነዚህን ሁለቱን ጨምሮ ሌሎችም ብሔራዊ ቁመና ላይ የተመሰረተ የተቃውሞ ፖለቲካ እንቅስቃሴ በማድረግ የሚታወቁ የድርድሩ ተሳታፊ ፓርቲዎች

የሚያነሱት ጥያቄ በሕ-መንግስታዊ ማዕቀፍ ውስጥ የሚመለስ እንጂ ያን ያህልም የከረረና የመረረ ውዝግብ ሊያስከትል የሚችል አይደለም ባይነኝ፡፡ በአንፃሩ እነ መ.ኢ.አ.ድ እና ሰማያዊ ፓርቲ የተሰለፉበት የተቃውሞ ጎራ ድርድሩን አስመልክቶ የያዘው አቋም ሲታይ በሕገ-መንግስታችን ከተደነገገ የፖለቲካዊ ችግር አፈታት ማዕቀፎች ያፈነገጠ የሚያስመስለው አዝማማያ ይስተዋልበታል ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ አስተያየቴ ምክንያት የሆነኝም የመ.ኢ.አ.ድ.ፕሬዚዳንት ዶክተር በዛብህ ደምሴና እንዲሁም ደግሞ አዲሱ የሰማያዊ ፓርቲ አቻቸው አቶ የሺዋስ አሰፋ የድርድሩን ሒደት አስመልክተው፣ በተለይ ለአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ የአማርኛው ክፍል የሰጡት ማብራያ ነው፡፡

እንዲያውም እውነቱን ለመናገር ሁለቱ የተቃዋሚ ፓርቲ ፕሬዚዳንቶች የድርድሩን መርሐ-ግብር አስመልክተው በተለያየ ቀን ለአሜሪካ ድምፅ የአዲስ አበባ ዘጋቢ ለመለስካቸው አምሃ የሰጡት ከአንድ ምንጭ የተቀዳ የሚመስል ማብራሪያ፣ ውጭ ያሉት እነ ግንቦት ሰባትና እነ ኦ.ነ.ግ ከሚያሰሙት የጦር አውድድ ቅኝት የተላበሰ ጩኸት እንብዛም የተለየ እንዳልነበር ነው ማስታወስ የሚቻለው፡፡ ለምሳሌ የመ.ኢ.አ.ድ.ፕሬዚዳንት ዶክተር በዛብህ ደምሴ ገና ድርድሩን መኖር የሰማንበት የመጀመሪያው ዜና መደመጡን ተከትሎ ለሬድዬ ጣያው በሰጡት ማብራሪያ “ምንም እንኳን እኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደኢህአዴግ መሳሪያም ገንዘብም ባይኖረንም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ከኛ ጋር ነው፡፡ ህዝቡ ከኛ ጎን የተሰለፈ መሆኑን በደንብ ከመረዳታቸው የተነሳም ነው መንግስት ያለወትሮው ኑና እንደራደር የሚል ጥያቄ ለማቅረብ የተገደደው” ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

እርሳቸው ይህን እንደ መኩራራት የሚቃጣው ንግግር ካስደመጡ ከጥቂት ቀናት በሁዋላ የሬድዮ ጣቢያው (የቪ.ኦ.ኤ) ተረኛ እንግዳ ሆነው የቀረቡት የሰማያዊ ፓርቲ ፕሬዚዳንት፣ አቶ የሺዋስ አሰፋም እንዲሁ “ኢህአዱግ እንደራደር የሚል ጥያቄ ያቀረበልን እርሱ ስለፈለገ ሳይን ህዝቡ እኛ አንተን አልመረጥንህምና ይልቅ ስልጣን ማስረከብ አለብህ ብሎ ቁርጠኛ አቋሙን ስለገለፀለት ነው” ሲሉ ተመሳሳይ ሃሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ገዥው ፓርቲ ከዚህ ቀደም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ለሚያቀርቡለት የ“እንደራደር” ጥያቄ በሩን የመከፈት ፍላጎት አሳይቶ እንደማያውቅ የገለፁት አቶ የሺዋስ ከኢትዮጵያ ህዝብ ሰባ በመቶ የሚሆነው፣ ኢህአዴግ በምርጫ አሸንፌያለሁ እያለ ሲናገር ለሚደመጠው የማስተማመኛ ድምፁን የነፈገበትን የተቃውሞ ሰልፍ እንዳካሔደ ደፍሮ መናገር ይቻላል” ሲሉ

የመ.ኢ.አ.ድ ፕሬዚዳንት ያንፀባረቁትን አቋም የመድገም ያህል በሚቆጠር መኩራራት ሃሳቡን ለማጠናከር ሞክረዋል፡፡

አቶ የሺዋስ አሰፋ እንዲህ ሲሉ በአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ ጣቢያ የተደመጡበት ንግግር ፓርቲያቸው በድርድሩ ዙሪያ ለሀገር ውስጥ ሚዲያዎች የሰጠውን ጋዜጣዊ መግለጫ በመሩበት መድረክ ላይ እንደሆነም ነው ዘገባው ያመለከተው፡፡ እናም "ስለዚህም ሰማያዊ ፓርቲ ድርድሩ እኛን ብቻ ሳይሆን ኢህአዴግ በሽብርተኝነት የፈረጃቸውን ተቃዋሚዎች ጭምር እንዲያካትት ይጠይቃል" የሚል አቋማቸውን አክለው አንፀባርቀዋል ፕሬዚዳንቱ አቶ የሺዋስ አሰፋ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፡፡ ታዲያ ከዚህ የተቃውሞው ጎራ ፖለቲከኞች ሰሞነኛ ፕሮፓጋንዳ አኳያ ሲታይ የፓርቲዎቹ ድርድር ምን ከእስከዛሬው የተለየ ውጤት ያመጣል ብለን እንጠብቅ ይሆን?

ደግሞስ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ እነርሱ እንደሚሉት ለመሰል ድርድር አዲስ ነውን? ገና ከትጥቅ ትግሉ ዘመን ጀምሮ ከደርግ ኢ.ሰ.ፓ ጋር ጭምር የተደራደረበትን የሎንደኑንን ጉባኤና እንዲሁም ከኦ.ነ.ግ እስከ መ.ኢ.አ.ድ በየወቅቱ ላቀረቡለት የ"እንደራደር" ጥያቄ አውንታዊ ምላሽ በመስጠት የዚች አገር ፖለቲካዊ ችግሮች በውይይት ይፈቱ ዘንድ የበኩሉን ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን የምናውቀው ጉዳይ አይደለምን? እውን ከፅንፈኞቹ የሀገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች ይልቅ ኢህአዴግ ነው የሰላማዊ ውይይት ፀር ተደርጎ መወሰድ ያለበት? እኔ ይሄን ወቀሳቸውን ፈፅሞ አልቀበለውም፡፡

ለማንኛውም ግን፣ ውይይቱ ወይም ድርድሩ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የየራሳቸውን ሃላፊነት መወጣት እንደሚኖርባቸው ሊሰመርበት ይገባል፡፡ እናም ከዚህ በመነሳት መላው ሰላም ወዳድ ህብረተሰባችን ጉዳዩን ከመቸውም ጊዜ በተሻለ ትኩረት ሊከታተለውና የጋራ ቤታችን ናት የምንላትን አገራችንን ወደ ለየለት የብተና አደጋ ለሚወስድ ትርምስ በማጋለጥ የሚገኙን ፖለቲካዊ ትርፍ ብቻ የሚያሰሉ ተቃዋሚ ቡድኖች ላይ ትርጉም ያለው ተፅዕኖ ለማሳደር የሚችል ገንቢ ሚናውን መጫወት ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም ህዝቡ በቸልታ መንፈስ መመልከቱን አቁሞ ይህን ጉዳይ ኢትዮጵያዊያን መክረን ዘክረን ህጋዊና ሰላማዊ መፍትሔ ልናበጅለት እንደሚገባ ማስገንዘብ ካልተቻለ በስተቀር እቺን አገር የነሶሪያ እጣ እንዲገጥማት ለማድረግ ቆርጠው የተነሱ ፅንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ከእኩይ ተግባራቸው ይታቀባሉ ብሎ ማሰብ ተራ የዋህነት ይሆናልና ነው፡፡

በተለይም ደግሞ፣ የተቃውሞውን ጎራ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚደግፉ ዜጎቻችን ዛሬ እንኳን ቆም ብለው አመለካከታቸውን በቅጡ ለመፈተሽና የአገራቸውን ህዝቦች በብሔር ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሽፋን እርስ በእርስ የማናቆር ዓላማ አንግበው ለሚንቀሳቀሱ የጥፋት ሃይሎች ድብቅ አጀንዳ ማስፈፀሚያ የሚሆኑበት ምንም ዓይነት ምክንያት እንደሌለ መገንዘብ እንደሚኖርባቸው ነው የሚሰማኝ፡፡ ፓርቲዎቹ አገራችን የምትመራበት ህገ-መንግስት ላይ የተደነገገውን የሰላማዊ ትግል ማእቀፍ አክብረው በመንቀሳቀስ ብቻ የፖለቲካ ስልጣን ለመጨበጥ እንዲችሉ ወደየራሳቸው ውስጣዊ ድክመት ቢመለከቱና መሰረታዊ ችግሮቻቸውን የመፍታት ጥረት ቢያደርጉ እንደሚመረጥ ደጋፊዎቻቸው ሊነግሯቸው ይገባል ባይ ነኝ እኔ በግሌ፡፡

በዚህ መልኩ መገለፅ ያለበት የህብረተሰቡ ገንቢ ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግስ በበኩሉ ማድረግ የሚገባው ጉዳይ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርምና እርሱን በመመለስ ሃሳቤን ላጠቃል፡፡ ስለዚህ እንደእኔ እምነት ከሆነ፣ ኢህአዲግን የሚመለከተው የቤት ስራ ከሁሉም ወገኖች ይልቅ ሆድ ማስፋትን የሚጠይቅና ግን ደግሞ የስርዓቱን አሳሳቢ አደጋዎች ሰው ሰራሽ ገፅታ መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች እንዲረዱለት የማድረግ ሃላፊነቱን መወጣት መቻል ነው፡፡ በተረፈ ግን ሊካሄድ የታሰበው ውይይት አሊያም ደግሞ ድርድር የተቃና ይሆን ዘንድ ልባዊ ምኞቴን ከወዲሁ እገልፃለሁ፡፡

መዐሰላማት!